# ወገንተኛ ያልሆነው የጋዜጠኞች መድረክ

ሙለጌታ አባተ

04/03/14

ይህ ጽሁፍ ኢትዮ ምሕዳር ጋዜጣ በመጋቢት ወር እትሙ "ከማንም ያልወገነ የጋዜጠኛ ማህበር ያስፈልገናል" በሚል ነጥብ ዙሪያ መምህርና ጋዜጠኛ ከነበሩት አያሌው አሥረስ ጋር ስላደረገው ቃለ ምልልስ ይመለከታል፡፡ በቅድሚያ አያሌው አሥረስ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ይሰሩ እንደነበርና ኋላም ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ መልቀቃቸውን ይነግሩናል፤ ቀጥሎም ወደ ግሉ ፕሬስ መግባታቸውን እንዲሁ፡፡

እርግጥ ነው፤ ኢሕአዴግ ወደ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሥር በሚታተሙት አዲስ ዘመን፤ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያን ሔራልድ፤ አልዓለምና በሪሣ ጋዜጦችና የካቲት መጽሄት እንዲሁም በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቭዥን በጋዜጠኝነትና በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ይሰሩ የነበሩ የተወሰኑ ጋዜጠኞች ከአጠቃላዩ ሠራተኛው ጋር በተደረገ ውይይትና ግምገማ ከሥራና ከኃላፊነታቸው እንዲለቁ ተደርገዋል፡፡

እዚህ ላይ ቅሬታውንና ፊፀሙ የተባሉትን በደል ወይንም የአስተዳደር መዛባት አድልዎ ያቀረቡት የየሚዲያ ተቋማቱ ሠራተኞች መሆናቸውን ልብ እንበል፡፡ እነዚሁ ነባር ጋዜጠኞች ደግሞ በንጉሱ ዘመን የተመሠረተውና አሁን 45ኛ ዓመቱን ለማክበር በመዘጋጀት ላይ ያለው የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር ቁልፍ አመራርና አባላት የነበሩ መሆናቸው ሳይዘነጋ፡፡

እነዚህ በኢጋማ አመራር አባልነታቸው በውጭ ካሉ ዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች ማህበራትና ተቋማት ጋር ሰፊ ግንኙነት ለመመሥረት በወቅቱም ለስብሰባ በሚል ብዙ አገራትን የመጎብኘት እድል አግኝተዋል፡፡

ራስ መኮንን ድልድይ ፊት ለፊት ባለው ሕንፃ የመጨረሻ ፎቅ ላይም "የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር" የሚለው መለያ ምልክት በንጉሱም ሆነ በደርግ ዘመን ለእይታ ተሰቅሎ

እንደነበር የምናስታውሰው ነው፡፡ በተንጣለለው ቢሮ ውስጥ ማታ ማታ ጋዜጠኞችና ኃላፊዎች የሚዝናኑበትና ቢራ የሚጎነጩበት የመዝናኛ ክበብም ነበራቸው፡፡ ይህን ማህበር በዚያን ዘመን ታዋቂ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች መርተውታል፡፡ ለማህበሩ መዋጮ ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ይቆረጥም ነበር፡፡

አብዛኛው የትምህርት እድል ሥልጠናና የሥራ ጉብኝት እድል የሚመጣው ከወቅቱ የምሥራቁ ዓለም የሶሻሊስት መንግሥታት ሶቪየት ሕብረት፣ ምሥራቅ ጀርመን፣ ቼኮዝላቫኪያ፣ ቡልጋሪያ፣ ሩማኒያ፣ ኩባ፣ ሰሜን ኮሪያና ሌሎችም ሀገራት ነበር፡፡ በዚህም በርካታ ጋዜጠኞች የዕድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በልምድ ልውውጡም እውቀት ቀስመውበታል፡፡ የተገኘውን እውቀት ምን ያህል ሥራ ላይ እንዳዋሉት ባይታወቅም፡፡

በዚያን ወቅት በሀገሪቱ አንድ የጋዜጠኛ ማህበር ብቻ ሲኖር አመራሩ ሆኑ አባላቱም ፍጹም ወገንተኝነታቸው ለመንግሥትና ለፓርቲው ብቻ ነበር - ለኢሠፓ፡፡ ይህንን እውነት የዛሬዎቹ ወገንተኛ ስላልሆነ ማህበር አፋቸውን ሞልተው ሊነግሩን የሚሞክሩት አዛውንቶቹ ጋዜጠኞች መቼም ይክዱታል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ሳንሱር አድራጊዎቹም እነሱው፤ የተለየ የዴሞክራሲ ድምጽ ወይንም አማራጭ በሚሉ ወገኖችም ላይ የሚዘምቱት በግንባር ቀደምትነት እነሱው ነበሩና ነው፡፡ በሀገሪቱም የሳንሱር ህግ የነበረ ከመሆኑ አንጻር እንደ ዛሬው እንደ ልብ መጻፍ፤ መተቸት፤ መውቀስ፤ ማጋለጥ ጭርሱንም አይታሰብም፡፡ ከሥራ መባረርና እስከ እሥር ቤትና የሕይወት መስዋዕትነት ድረስ የሚያስከፍል በመሆኑ በፍጹም ወገንተኝነትና ሎሌነት መንግሥትንና ፓርቲውን ጭምር ማገልገል ቀዳሚ ግዴታቸው ነበር፡፡

በዚያን ወቅት አማራጭ የዴሞክራሲ ድምጽ ሆነው በተነሱ የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥም የነበሩ በኋላም ሌሎቹ ሲፈርሱና ሲበተኑ በአንድ ጥላ ሥር ሆነው በእነዚያኞቹ ላይ ሰፊ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻና የሥነ ልቦና ጦርነት በኢሕአፓና መኢሶን እንዲሁም በሌሎች ላይ ያወጁት ዛሬም ድረስ በሀገር ውስጥ ያሉና በስደት ላይ የሚገኙት እነዚያው ጋዜጠኞች ናቸው፡፡

ዛሬ ደርሰው የፕሬስና የዴሞክራሲ ተሚጋች፤ የሰብዓዊ መብት ጠበቃ ነን ሲሉ መስማት አንከትክቶ ያስቃል፡፡ ለማያውቅሽ ታጠኚ የሚለው ሀገርኛ ተረት ለእነሱ ብጤዎች መሆኑ ነው፡፡

ስንቶች ሲሰደዱ፤ ከሥራ ሲባረሩ ለአብነት ታላቁ ደራሲና ጋዜጠኛ በአሉ ግርማ እንደወጣ ሲቀርና ደብዛው ሲጠፋ እነሙሉጌታ ሉሌ፣ እነ ክፍሌ ሙላት፣ እነ ማዕረጉ በዛብህ፣ እነ ከፍያለው ማሞ፣ እነ ጎሹ አበጀ እንዲሁም ዛሬ ወገንተኛ ያልሆነ ማህበር እናቋቁማለን ብለው ሰውን በየቦታው የሚያስተባብሩት እነ አያሌው አሥረስና እሸቴ ደስታ ሌሎችም አዲስ አበባ ላይ ነበሩ፡፡

በስደት ላይ የሚገኙት ሀገር ቤት ላሉት አያሌው አሥረስና እሸቴ ደስታ እንዲሁም ሌሎች በሚሰጧቸው ትዕዛዝና መመሪያ እንዲሁም የፋይናንስ ድጎማ መሠረት የቀለም አብዮቱን ለማቀጣጠል ከታቀደውና ከተያዘው አንዱ ፕሮግራም የእነሱን ዓላማ የሚያራምድና ሎሌያቸው የሆነ የጋዜጠኛ ማህበር መመሥረት ነው፤ ይህንኑ ለማሳካትም ተንቀሳቅሰዋል፡፡

ሥራ ለፈቱ ጋዜጠኞች የገንዘብ ድጋፍ ይደረግላችኋል፤ በቅርቡ ሥራ በሚጀምሩ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች ውስጥም ትቀጠራላችሁ ተብሎ ቃል ተገብቶላቸዋል፡፡ አሁንም ለአብዛኞቹ የቀድሞ ጋዜጠኞች በአሜሪካ ለሚገኙ የተቃዋሚ ራዲዮ ጣቢያዎች ኢሣትን ጨምሮ በሪፖርተርነት ሞቅ ያለ ገንዘብ እየከፈሉ እንደሚያሰሯቸውም ይታወቃል፡፡ የነ አያሌው አሥረስና እሸቴ ደስታ አዲሱ ወገንተኛ ያልሆነ ማህበር ማለት እንግዲህ ይህ ነው፡፡

አሁንም ወገንተኛ ያልሆነ ጋዜጠኛ ማህበር ያስፈልጋል፤ ያሉት ማህበራት ደካማዎችና በመንግሥት የተጠለፉ ናቸው በማለት ያለ አንዳች ሃፍረት በሀገር ውስጥና በውጭ የሚጮሁት እነዚሁ አንጋፋ የሚባሉት ጋዜጠኞች ናቸው፡፡

ትናንት የኢትዮጵያን ሚዲያ አመራር ሲፈነጩበት፤ ጋዜጣውን፣ ራዲዮንና ቴሌቪዥኑን ይዘው እንዳሻቸው ሲያዙበት ኖረዋል፡፡ ሰውን አስደግድገዋል፡፡ ያሻቸውን ሲሰሩ፣ ሲፈልጡና ሲቆርጡ ኖረዋል፡፡ ከሥራና ከኃላፊነታቸው ተነስተው ስለወረዱ ብቻ ዛሬ በኢትዮጵያ ራዲዮ ወይንም ቴሌቪዥን ወይንም በመንግሥት መገናኛ ብዙሀን ሲጠየቅ

መልስ የሰጠ ወይንም ቀርቦ የተናገረ ሰው ውጉዝ ከመአርዮስ፣ ተለጣፊ፣ ኢህአዴግ፣ በገንዘብ የተገዛ ነው እያሉ የዘቀጠ ፕሮፓጋንዳ የሚነዙት፡፡

ምን ይህ ብቻ፡፡ ወጣቱንም ተተኪ ትውልድ በጭፍን ጥላቻ የሚያጠምቁት፣ ለመንግሥት ያደረ ነው ብለው የስም ማጥፋት ዘመቻና ስብዕናን የመግደል የፈጠራ አሉባልታ እየነዙ የሚያሰራጩት፡፡ አዲሱንም ተተኪ ትውልድ እየመረዙ የጥላቻና የበቀል መርዝ እየጋቱ፣ በሽፋን የራሳቸውን በቀል መወጫ ያደረጉት - እነዚሁ ናቸው፡፡

በንጉሱም ሆነ በደርግ ዘመን የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር አመራር በነበሩበት ወቅት ለጋዜጠኛው የተከራከሩበት፣ የቆሙለት፣ የተሟገቱለት አንድም ምንም ነገር የለም፡፡ ጭርሱንም ከጋዜጠኝነታቸው ባሻገር ቁልፍ የአመራር ቦታዎችን በፕሬስ፣ በራዲዮና በኢቲቪ ውስጥ በመያዛቸው የተነሳ ጋዜጠኛውን በአስተዳደራዊ ጫና እድገት በመንፈግ፣ ወደ ክፍለ ሀገር በማዛወር፣ ከሥራ በማሰናበት፣ በጎጠኝነት ስሜትም የየራሳቸውን የአካባቢ ሰው በመቅጠርና ሌላውን ደግሞ በማስፈራራት ደም እምባ ሲያለቅሱት ኖረዋል - ለዚህም ዛሬ በሥራና በህይወት ያሉ ሰዎች ምስክሮች ነው፡፡

ለተላላኪዎቻቸው፣ ለእቁባቶቻቸው፣ ለወሬ አቀባዮቻቸው የተሻለ ቦታ መስጠት፣ በፍጹም አምባገነንነት በሙያውም በሥራውም ላይ ፈንጭተውበት አልፈዋል፡፡ ዛሬ በአገር ውስጥ ያሉት ወኪሎቻቸውና በስደትም ያሉት ደርሶ የዴሞክራሲ ጠበቃ፣ የፕሬስ ነጻነት ተሟጋች፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ወገንተኛ ያልሆነ ማህበር አፈ ቀላጤ ሆነው ለመታየት ትያትር ሲሰሩና ሲተውኑ ማየት ከአንጀት አንከትክቶ ያስቃል፣ ያስደምማል፡፡

ዛሬ ባህር ማዶ ያለውን የጽንፈኛና የጥላቻ ሚዲያ በበላይነት የሚመሩትም እነሱው ናቸው፡፡ ከሁሉ የከፋው ያንኑ ሴረኛና መርዘኛ ትውልድ በካይ ጭፍን የጥላቻ ፖለቲካና የጎጠኝነት ባህርያቸውን ተሸክመው በስሜታዊነትና በግልብነት ታጅበው የጥፋት ድግስ ቀማሪና ስትራቴጂስት ሆነው ቆዳቸውን ለውጠው መቅረባቸው ነው፡፡

የዚህ ሁሉ መነሻ፣ ረዥም ርቀት ሄደው ሙያውን በመጠቀም የማያባራ ጦርነት የከፈቱበት ምክንያት ለምን ኢሕአዴግ ከሥራችን አባረረን በሚል ለመበቀል ቆርጠው በመነሳታቸው እንጂ ለፕሬስ ነጻነት ተቆርቋሪ ሆነው አይደለም፡፡ እነሱ ቁልፍ ቦታ በነበራቸው ዘመን ጋዜጠኛው ሲዋከብ በተጠርጣሪነት ሲታሰር፣ የደረሰበት ደብዛው ሲጠፋ እንኳን

በማህበራቸው ድምጽ ሊያሰሙ ቀርቶ ትንፋሽ አላሉም፡፡ ዘመን ካለፈ በኋላ በእጅ መንሻነት ለማቅረብ የሞከሩትም አላዋጣም፡፡

ከሥራቸው ባይፈናቀሉ ኖሮም ታማኝነታቸውን አረጋግጠው ከበሮ መደለቁን ይቀጥሉበት ነበር፡፡ ከሥራቸው ከወጡ በኋላ በሀገሪቱ የፕሬስ ነጻነት መታወጁና ሙያው ስላላቸው የግል ጋዜጣና መጽሄት አሳትሞ ለመሸጥ ቀዳሚ ሆኑ፡፡ የወቅቱ የፖለቲካ ውጥረትና አለመረጋጋት፣ ከሕዝቡ ምን አዲስ ነገር አለ ከሚለውና ለማወቅ ከነበረው ፍላጎት አንጻር ገበያውን ማግኘት ቻሉ፡፡ በርካታ ወጣቶችም ባላቸው የጋዜጠኝነት ዝንባሌ የግሉን ፕሬስ ተቀላቀሉ፡፡

ለሙያው ሥነ ምግባር መከበር ተምሣሌት መሆን የነበረባቸው እነዚሁ ጋዜጠኞች ጋዜጣና መጽሔቱን ቀጥተኛ ጦርነትና ግብግብ መግጠሚያ ጦር ሜዳ አደረጉት፡፡ በቀላቸውን ለመወጣት ትልቅና ሰፊ አጋጣሚ እንዲሁም የጦር መሣሪያ በእጃቸው የገባ ያህል አድርገው ወሰዱት፡፡

አዲሱና የግሉን ፕሬስ የተቀላቀለው በእነሱ ተንኮልና መሰሪ ሴራ ሥር ያላለፈው ወጣት በእድሜ አንጋፋነታቸውና በነባር ጋዜጠኝነታቸው አክብሮት ነበረው፡፡ ቢሆንም ከእነሱ ውጪ ያለውን አብዛኛውን የግል ጋዜጣ በመንግሥት የሚደገፍ ነው በሚል በውጭ ራዲዮ ጣቢያ እንዲተላለፍ በማድረጋቸው የሌሎች ጋዜጦች ገበያ እንዲያጣ ገበያው ወደ እነሱ ብቻ እንዲገባ የከፋ የመሰሪነት ሥውር ሥራ ሰሩ፡፡ ይህም ብዙ ግጭት አስከተለ፡፡

በግሉ ፕሬስ በሚወጡ ዘገባዎች የሕግ ተጠያቂነት በመምጣቱና የግል ጋዜጠኞች በመታሰራቸው ድምጽ የሚያሰማ ማህበር  መፈጠር አለበት ተብሎ ወደ ሃያ የሚጠጉ ሰዎች ተሰባሰቡ፡፡ ለምን ሁለት ማህበር ያስፈልጋል፣ ጋዜጠኛው በሙያው አንድ ነው፣ የመንግሥትና የግል ማለቱ ይቅርና በአንድ ላይ እንሁን የሚል ተደጋጋሚ ውይይትና ስብሰባ ተደረገ፡፡

ትናንት ከመንግሥት ጋዜጠኝነት በመልቀቃቸውና ከኃላፊነት ቦታም በመነሳታቸው ጋዜጠኛውም ብሶቱን በአደባባይ በማሰማት ሰለሞገታቸው ይህንን በበቀልና በቂምነት የያዙት ስለሆነ ከመንግሥት ጋዜጠኛ ጋር እንዴት አንድ ላይ እንሆናለን፣ የመንግሥት

አገልጋይ ነው፤ እናም አብረን ማዕድ አንቆርስም፤ አብረንም አንሰራም፤ ጠላቶች ማለት ነን አሉ፡፡

በዚህም መሠረት ትናንት ይመሩት ከነበረው ኢ.ጋማ (የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር) ብዙም ሳይርቁ ‹‹ነ›› የተባለችውን ፊደል ጨምረው ኢነጋማን (የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበርን) አቋቋሙ፡፡ እንደተለመደው አመራሩንም፤ የውጭ ግንኙነቱንም በመቆጣጠር ለበርካታ ዓመታት እንዳሻቸው በፍጹም አምባገነንነት እየተፈራረቁ መሩት፡፡

የአውሮፓን ጉዞ የውኃ መንገድ አደረጉት፡፡ በታሰረው ጋዜጠኛ ስም መግለጫ በማውጣትና የውጭ እርዳታ በመሰብሰብ በዲያስፖራ ካለውም ኢትዮጵያዊ በመለመን፤ ለታሳሪ ቤተሰቦች፤ ለጠበቃ፤ ለፍርድ ቤት ዋስትና፤ ታሳሪዎቹን ለመጠየቅ በሚል ቁጥር ላይ የለሽ ዶላር ሰበሰቡ፡፡ ገንዘቡንም የሚቀበሉት የሚያስቀምጡት በግል አካውንታቸው ነው፤ ጠያቂም፤ ተቆጣጣሪም አልነበራቸውም፡፡

ማህበሩ ሕጋዊ ፈቃድ ለስምንት ዓመታት ስላልነበረው የሕግ ግዴታና ተጠያቂነት አንዷትም አለመኖሩ የበለጠ አመቻቿቸዋል፡፡ አሜሪካና አውሮፓ በማህበር ስም የሚሰበስቡትም ገቢ የሚደረገው በግል አካውንታቸው ከመሆኑም ሌላ ታሳሪዎቹ ሲለቀቁ ለዋስትና የተያዘው ገንዘብ ተለቆ የሚገባው በግል ኪሳቸው ይከተታል፡፡

የግል ጋዜጠኛ ሲታሰር መግለጫ አውጥተው ለኤምባሲና ለውጭ ሀገር ተቋማት የሚበትኑት ወዲያውኑ ይህን ተከትሎ ከፍተኛ ገንዘብ ስለሚላክ ለእነሱ የጦፈ ንግድ ነበር፡፡ ምስኪኑ ጋዜጠኛ ግን ከመከራና ሥቃይ በስተቀር፤ በስሙ ከመነገዱ በስተቀር የሚያየውም የሚደርሰውም ነገር አልነበረም፡፡ ታመው መታከሚያ ገንዘብ በማጣት የሞቱ የግል ጋዜጠኞች፤ ዋስትና በማጣት ራሱን ያጠፋ ጋዜጠኛም ነበር፡፡

በአንፃሩ እነሱ ግን ቤት ሰርተዋል፤ የግል መኪና፤ ታክሲ፤ ሱቅም በዘመድ አዝማድ ስም ከፍተው ነግደዋል፤ አስነግደዋል፡፡ ጋዜጠኛ ያልሆኑትንና ወዳጆቻቸው የሆኑትን ሰዎች ሌሎችንም እንደሚሄዱት ሀገር ርቀት በወቅቱ እየተሰላ ገንዘብም እየተቀበሉ በማህተም አትመው ማስረጃ በመስጠት በማህበርና ምንም በሌለው የግሉ ጋዜጠኛ ስም በመጠቀም የሰዎች ንግድ በከፍተኛ ደረጃ አካሂደዋል፡፡

የጋዜጠኛው ብሶትና መከራ በስሙ መነገዱ አስቆጥቶት ሊታገላቸው ሲነሳ በለመዱትና በኖሩበት የስም ማጥፋት ዘመቻ መሠረት ይህ የወያኔ ሰርጎ ገቦች ማህበሩን ለማፍረስ የሚያደርጉት ሴራ ነው በሚል እጃቸው ላይ በነበሩት ጋዜጦችና ባህር ማዶ በሚሰራጩት የተቃዋሚ ራዲዮ ጣቢያዎች በመጠቀም ፀንተው በታገሏቸው ላይ ከመግደልና ከማስገደል ያልተናነሰ መጠነ ሰፊ የስም ማጥፋት ዘመቻ አካሂደዋል፡፡ ምክንያታቸው ግልጽ ነው፡፡ ሰፊ ጥቅምና የተካኑበትን ማጭበርበር ስለሚያጡት ነበር፡፡

ከሀገር ወጥተው በስደት በሄዱበት አሜሪካም ሆነው ሀገር ውስጥ ላሉ  መረጃ አቀባዮቻቸው ወርሃዊ መደበኛ ደመወዝ በመመደብ  እየተወራጩ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ነበሩ የፕሬስ ነጻነት ተሟጋቾች፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች፣ የመናገር ነጻነት ጠበቃዎች ነን እያሉ ሲመፃደቁ የነበሩት፡፡

የ97 ምርጫ ሲመጣ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለይቶላቸው ከገለልተኛ ማህበርነት ይልቅ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ተሰልፈው፣ የሲቪክ ማህበራት ዋና ጸሀፊም ሆነው በግልጽ የፖለቲካ አሰላለፍ ቆመው የግሉ ፕሬስ የተቃዋሚው ልሣንና የአመጽ ቀስቃሽ በመሆን እንዲቆም አድርገውታል፡፡ ዛሬም ከቀጣዩ ምርጫ በፊት የግሉን ፕሬስ ከጀርባ በመጠቀም በገንዘብ በመደገፍ የአመጽና የሁከት መቀስቀሻ መሣሪያ አድርገው እየተጠቀሙበትና አይዞህ ግፋ እኛ አለንልህ እያሉት ነው፡፡

ዛሬም አሜሪካ ሆነው የግንቦት ሰባቱን ኢሣት የሳተላይት ቴሌቪዥን በመመሥረት በዋና ተዋናይነት እያሽረገዱ ነው፣ አብዛኛዎቹ የግል መጽሄቶችና አንዳንድ የግል ጋዜጦች ያለጥርጥር እነሱን...እነሱን የሚሸቱበት ታሪክም ይኸው ነው፡፡

ቀጣዩ ምርጫ ስለደረሰም ሙቀቱን ከፍ የሚያደርግ የጋዜጠኞች መድረክ የሚል ማህበር እንዲቋቋም ድርጅታዊ ትዕዛዙ  የመጣው ከባህር ማዶ ነው፡፡ እናም አያሌው አሥረስም ሆኑ እሸቱ ደስታ እግራቸው እስኪቀጥን እየዞሩ ለቀድሞ አባላት እባካችሁ በአዲስ መልክ እንሰባሰብና እንስራ፣ የገንዘብ ችግር የለም፣ ሥራ ለሌላቸውም ሥራ እንከፍታለን፣ ገንዘብም እንረዳለን እያሉ ሲማፀኑ የነበረው፡፡

ለኢትዮ ምሕዳር ጋዜጣ አያሌው አሥረስ በገለፁት መሠረት ይህን የመሰለ ወገንተኛ ያልሆነ የጋዜጠኛ ማህበር ለማቋቋም ነው አመራር የመረጡት፡፡ እንግሊዝና አሜሪካ

ኤምባሲ ተወካዮች የተገኙላቸው የቀለም አብዮቱን ለመምራት የተመረጡና የተመለመሉ ጎበዞች በመሆናቸው ነው፡፡ ፌዝ ነው አሉ ሲዳሩ ማልቀስ፡፡ እንዲህም አድርጎ ወገንተኛ ያልሆነ ማህበር የለም፡፡

የግል መብታቸውን ብናከበርም፤ ጋዜጠኛ አያሌው አፅረስ መጀመሪያ የመአሕድ አባል፤ መአሕድ ሲፈርስ የመኢአድ አባል፤ በኋላ ደግሞ የቅንጅቱ አመራርና አስተባባሪ፤ ቅንጅቱ ሲፈርስ ደግሞ የአንድነት አባልና ‹‹የነጋድራስ የግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ መሆናቸውን ድፍን ሀገር ያውቃል፡ አያሌውና መሰሎቹ ወገንተኛ ስላለመሆን ማውራት አይችሉም፡፡

በአጭሩ በሀገር ውስጥ ባለው ተቀዋሚ የፖለቲካ ፓርቲና በዲያስፖራው ጽንፈኛ ተቃዋሚ የተደራጀና የሚመራ በገንዘብም የሚደገፍ የጋዜጠኞች መድረክ አቋቁመናል፤ ምርጫ አድርገናል ማለትም ይችላሉ፡፡ ከዚህ በላይ ወገንተኝነት የለም፤ ሊኖርም አይችልም - ድንቄም፡፡